**BRIGGS CENTER**
FOR FAITH & ACTION

# ስለ ቲፒኤስ አጠቃላይ እይታ¨ በፍሬው ሃይሌ
# (የኢሚግሬሺን ህግ አገልግሎት ክፍል ሃላፊ)

ቲፒኤስ ወይንም Temporary Protected Status (TPS) በተፈጥሮና ስው ሰራሺ አደጋ፤ የሃገር ስላምና ደህንነት ሁኔታዎች መደፍረስ አሊያም ክባድ ሁኔታዎች በሀገር ላይ ተፈጥሮ የዚያች ሀገር ዜጎች በአሜሪካን ሀገር ወስጥ በማናቸውም ምክንያት በማናቸውም የኢሚግሬሺን ስታተስ ቢሆኑ የሀገራችው ሁኔታ እስኪረጋጋ ወይንም መመለስ ለደህንነት አስጊ እስከማይሆንበት ጊዜ ድረስ በጊዚያዊነት በህጉ መልካም ፈቃድ ሀገሪቱ ውስጥ እንዲቆዩ የስራ ፈቃድና የጉዞ ሰነድ እንዲያገኙ የሚያስችል የህግ[1] አሰራር ሂደት ነው።

ሀገራትን ለዚህ ጊዚያዊ ለሆነ የኢሚግሬሺን ጥቅም በእጩነት የማቅረብ፤ማደስና የመስረዝ ስልጣኑን የሰጠዉ ለሀገር ውስጥ ደህንነት የበላይ አዛዥ (DHS) ነው። ቲፒኤስ ሀገራት በታጩበት ወቅት አሜሪካን ሀገር ውስጥ ያልነበሩ የእጩ ሀገራትን ዜጎች አይመለከትም።

እንደ ብዙዎቹ የኢምግሬሺን ጥቅማ ጥቅሞች የቲፒኤስንም ጥያቄዎች ተቀብሎ ውሳኔ የሚስጠው ሁላችንም የምናውቀው ዩኤስሲአይኤስ (USCIS) የተስኘው ድርጅት ነው።

በህጉ መስረት[2] ቲፒኤስ ከ6-18 ወራት የሚሆን የጊዜ ገደብ መኖሩ ጊዚያዊነቱን ያሳያል። ሆኖም ግን በህጉ መሰረትና ሀገራትን ለቲፒኤስ የሚደነግገው የመንግስት አካል በቃ እስካላለ ድረስ በየጊዜው በማደስ ለብዙ አመታት የኖሩ የቲፒኤስ ተጠቃሚ ሀገራተ ዜጎች አሉ[3]።

ለበለጠ መረጃና በአሁን ሰኣት የቲፒኤስ  ድንጋጌ ያላቸውን ሀገራትና ዝርዝር መረጃዎችን ለማየት ይህንን ይጫኑ[4]

የዚህም አጭር የቲፒኤስ ማብራሪያ አላማ በቅርቡ ኢትዮጵያ  በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ለቲፒኤስ ድንጋጌ የቀረበች በመሆኑ ሊያመለክቱ ፈልገው መረጃ ( ህጋዊና ትክክለኛ) ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ይጠቅም ዘንድ መስሪያቤታችን ለህብረተስቡ ይህንን መረጃና አገልግሎቱን ሲያቀርብ  የዘላቂ ሰላምና መረጋጋት ለመላው ኢትዮጵያዊያንና ቲፒኤስ ላለቸው ሀገራት በመመኘት ነው።

“በአሜሪካን የሚገኙ በእርስ በእርስ ገጭቱና የስብአዊ ቀውሱ ምክንያት በሰላም ወደ ሀገራቸው መመለስ የማይችሉ ኢትዮጵያዊያን ሁኔታው እስኪረጋጋ ህገ ወጥ ሳይሆኑ ሀገራችን ውስጥ መቆየት ይችላሉ”[5]

© Briggs Center for Faith & Action | info@BriggsCenter.org | www.BriggsCenter.org
5148 Massachusetts Ave, Bethesda, MD 20816 | 301-229-7725

በኦክቶበር 21፣2022 የዲኤችሱ ሃላፊ አቶ አሊሃንድሮ ማዮርከስ ክላይ የተናገሩት ንግግርና ውሳኔ ኢተዮጵያ ለዚህ ቲፒኤስ ለተስኘው ጊዚያዊ የኢሚግሬሺን መፍትሄ ተጠቃሚ አንድትሆን አደረገ። ይሄንን ተከትሎ በተለያዩ የኢሚግሬሺን ሰታተስ አይነት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን ለመርዳት የመንግስትንና የድርጅታችንን የገቢ መስፈርት ካሟሉ በነጻ ኣሊያም በዝቅተኛ ክፍያ ጥብቅና እንቆማለን።

## ቲፒኤስ ለማመልከት ምን ማሟላት ያስፈልጋል

እያንዳዱ አእመልካች የቲፒኤስ ተጠቃሚ ለመሆን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ይገኝበታል ልብ ይበሉ ቲፒኤስ እንደ ሌሎች የኢሚገሬሺን ጥቅሞች በጥቅል ወይም አንዱ የቤተሰብ አባል ፈቃዱን ስላገኘ በተዋረድ ለሌሎች ስለማይደርስ ሁሉም አእመልካች የራሱ ማመልከቻ ማስገባት አእለበት ማለት ነው።

1. ዜግነት

   ቲፒኤስን የሚመለከተው የህጉ ከፍል[6] መመልከት የሚቸሉት ለቲፒኤስ የተደነገጉ ሀገራት ዜጎች አሊያም ዜግነት የሌላቸው ሆነው ለቲፒኤስ የተደነገገ ሀገር ውስጥ የነበሩና ድንጋጌው ሲስጥ አሜሪካን ውስጥ የነበሩ ሰዎችን ብቻ ነው የሚመለከተው ይላል።  አገለገሎቱ ያለፈበትም ቢሆን እንደ ፓስፖርት ያሉ ዜግነትን የሚገልጹ ማሰረጃዎች ያስፈልጋሉ።

2. በአካል የመገኘት

   ቲፒኤስ በስባዊነት የሚስጥ ጊዚያዊ የኢሚግሬሺን ሺፋን ስለሆነ ፕሮግራሙ ለብዝበዛ እንዳይጋለጥ ቲፒኤስ ሲደነገግ ከመቼ ጀምሮ አሜሪካ ውስጥ የነበሩ ሰዎችን እነደሚመለክት አብሮ ቀኑ ይቆረጣል በኢትዮጵያ የቲፒኤስ ድንጋጌ ላይ ኦክቶበር 21 2022 አሜሪካ ውስጥ ያልነበሩ ኢትዮጵያዊያን ይህንን መስፈርት ማሟላት ስለማይችሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም ይህ በመርህ ደረጃ ያለው አንዳለ ሆኖ ውስን ሁኔታዎች አንድ ሰው ድንጋጌው ሲወጣ ድንገት ለአጭር ጊዜ ሀገሪቱ ውስጥ ባይኖር የህጉን አላማ የሚጥስ ካልሆነ ሊፈቀድለት ይችላል[7] ሰፋ ያለ ትንታኔው ክዚህ ጽሁፍ ኣላማ ውጪ ስለሆነ በግል መጠየቅ ይቸላሉ። አሜሪካ ውስጥ በተባለው ቀን ለመኖርዎ ማስረጃ ያስፈልገዎታል ደረሰኞች የኪራይ ውሎች ወዘተ

3. በመመሪያው  በተገለጸው ጊዜ ውሰጥ አሜሪካ ውስጥ የሚኖር መሆን

   ይሄ መስፈርት ሆን ተብሎ የተወሰኑ ቃናት ብቻ ቲፒኤስ ከመደንገጉ ቀደም ብሎ እንዲሆን ነው የሚደረገው

4. ወደ አሜሪካን እንዳይገቡ ከገቡም እንዳይኖሩ ሊያደርግ ክሚችል ነገር የተቆጠቡ (grounds of inadmissibility[8])
5. በቁሚነት የኢምግሬሺን ጥቅሞችን ክማመልከት ሊያግድ በሚችል ወንጀል (ፌለኒ) ወይም ከሁለት በላይ የደንብ መተላለፍ ( ምስዲሚነር) ሪከርድ ላይ አለመኖር[9]

6. በቋሚነት ጥገኝነትን የሚከለክለው የህጉ አካል ለቲፒኤስም ይዋል ሲል ዘርዝር ያሉ ጥገኝነትን ማመልከት የለባቸውም ከተባሉት ውስጥ በተወሰኑት ወንጀሎች ያልተሳተፉ መሆን ግድ ይላል፡

## የማመልከቻ ጊዜ

<u>ቲፒኤስ ድንጋጌው ከተወሰነ በሁዋላ ሌላ ዝርዝር ነገሮችን የሚገልጸው መመሪያ ሲወጣ ነው ማመልከት የሚቻለው የኢትዮጵያን ቲፒኤስ ድንጋጌ በተመለከተ አሁን ላይ መመሪያው ገና አልወጣም።</u>

## መሞላት ያለበት ፎርም

1. ፎርም I-821, Application for Temporary Protected Status[10] ካስፈላጊው መረጃ ጋር መላክ ይኖርበታል በተለምዶ ይህ ፎርም በፖስጣ ነበር የሚላከው በቅርቡ ኦንላይን ማስገባት ተጀምሯል ነገር ግን ይሄንና መሰል ዘረዘር ሁኔታዎችን መመሪያው ስላልወጣ ማናችንም አናውቅም
2. ፎርም I-765, Application for Employment Authorization, የስራ ፈቃድ ለሚፈልጉ
3. ፎርም I-131 requests for travel documents የጉዞ ሰነድ[11] ለሚፈልጉ
4. ፎርም I-912, Request for Fee Waiver[12] መክፈል ለማይችሉ ሰዎች

ፎርሞቹ የሚገኙበት ቦታ ዩኤስ ሲ አይ ኤስ ዌብሳይቱ ላይ በነጻ ትክክለኛውን ፎርም ያስቅምጣል በሂደት ላይ ያለ የጥገኝነት ጉዳይ አለኝ የስራ ፈቃድም አለኝ ማመልከቱ ይጠቅምኛል ወይ? ህጉ አይከለክልም ይቻላሉ የስራ ፈቃድ ካለዎት ቲፒኤሱንና የጉዞ ፈቃዱን ብቻ ሞልተው መላክ ይችላሉ

መመሪያው ሲወጣ አሊያም ማመልከት ሲቻል እንዴት አውቃለሁ?

በአቅራቢያዎ የሚገኝ ፈቃድ ያለው የኢሚግሪሺን ባለሙያ ያናግሩ አሊያም ይሄንን ሊንክ በመጫን በጎ አድራጎት ደርጅቶችን[13] ያማክሩ

የኛ ቢሮም ሁል ጊዜ በራችን ክፍት ነው https://www.BriggsCenter.org

Briggs Center for Faith & Action | 5148 Massachusetts Ave, Bethesda, MD 20816 | 301-229-7725 | admin@briggscenter.org አሊያም ferewhaile@briggscenter.org ላይ አጭር መልእክት በመላክ መከታተል ይችላሉ

[1] በ1990 የተደነገገውን  Immigration and Nationality Act (INA) § 244ን ይመልከቱ

[2] INA § 244(b)(2)ን ይመልከቱ

[3] የኤልሳቫዶር ዜጎች ከስላሳ አመታት በላይ ዛሬም ድረስ የቲፒኤስ ተጠቃሚዎች ናቸው ዝርዝር መረጃውን ለማየት ይህን ይጫኑ
https://www.uscis.gov/humanitarian/temporary-protected-status/temporary-protected-status-designated-country-el-salvador

[4] https://www.uscis.gov/humanitarian/temporary-protected-status

[5] https://www.dhs.gov/news/2022/10/21/dhs-designates-ethiopia-temporary-protected-status-18-months

[6] INA § 244(a)(1)ን ይመልከቱ

[7] 8 CFR § 244.1(3) ን ይመልከቱ

[8] INA § 212(a)(9)(C)ና INA § 244(c)(2)(B)(ii) and 8 CFR § 244.4(b) ያጣቅሱ

[9] 8 CFR § 244.4(a)ን ማየት ይችላሉ

[10] https://www.uscis.gov/i-821 for the I-821 ላይ ይገኛል

[11] https://www.uscis.gov/i-131 ላይ ይገኛል

[12] https://www.uscis.gov/i-912 ላይ ይገኛል

[13] https://cliniclegal.org/find-legal-help/affiliates/directory